# የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደንብ ማሻሻያ ቁጥር 553/2021

## 1. መግቢያ

1.1. የተሻሻለዉን የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደንብ ቁጥር 549/2013ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

1.2. የኢትዮጵያ ምርት ገበያ (ከዚህ በኋላ "የምርት ገበያ" በማባል ይጠቀሳል) በምርት ገበያዉ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 550/1999 አንቀጽ 12(10) መሠረት ይህንን ደንብ ማሻሻያ አዉጥቷል፡፡

1.3. ይህን ደንብ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 551/1999 አንቀጽ 6(3) በተሰጠዉ ስልጣን መሠረት ካፀደቀዉ በኋላ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

1.4. ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደንብ ማሻሻያ ቁጥር 553/2021" በማባል ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ማሻሻያ

የተሻሻለዉ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደንብ ቁጥር 549/2013 (ከዚህ በኋላ ደንብ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል) እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

(1) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 3.2.1.18 በደንቡ ንዑስ አንቀጽ 3.2.1 ስር ተጨምሯል፡፡

"3.2.1.18 በባለስልጣኑ መጽደቅ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ምርት ገበያው ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የክፍያ ተመኖችን በየጊዜው እንዳስፈላጊነቱ ያወጣል፡፡"

## 3. ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን

ይህ ማሻሻያ በደንቡ አንቀጽ 21.1 መስረት በባለስልጣኑ በፀደቀ በአስራ አራተኛዉ ቀን ህጋዊ ዉጤት ይኖረዋል፡፡

**በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ቦርድ**

**ሃምሌ 15 ቀን 2008 ዓ.ም በአዲስ አበባ ፀደቀ**